# በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

**መስከረም/2017ዓ.ም.**


## የግሉ ዘርፍ ድምጽ!

## ማውጫ


AFCFTA ብሄራዊ የትግበራ ኮሚቴን--1

የምስጋና ፕሮግራም————————————-—1

የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት———————-1

የእንኳን ደስ አልዎት መልዕክት————-———-1

ከአይ ኤም ኤፍ ልዑክ ጋር ውይይት————2

የኢትዮ ሻንዚ የንግድ ፎረም———————2

የAFCFTA ትግበራ ውይይት————-———3

ከአፍሪኤግዚም ባንክ ልዑክ ጋር ውይይት——4

ከሰላም ሚኒስቴር ተወካዮች ጋር ውይይት—-4

የአውሮፓ ከደን ጭፍጨፋ ነጻ ህግ ውይይት—5

በአቮካዶ፣ ሽንኩርትና አኩሪ አተር ዙሪያ——-7

ምክር ቤቱ ከጂ አይ ዜድ ጋር ውይይት————-7

የምክር ቤቱ ልዑክ በጋና ያደረገው ጉብኝት—-8

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ውይይት——————9

ከዋሽንግተን የሳይፕ ልዑክ ጋር ውይይት——9

የባለሙያዎች ዲጂታል ስልጠና——————-10

የኦሮሚያና ቱርክ ንግድ ምክር ቤቶች———11

አድራሻ———————————————12


## የእንኳን ደስ አለዎት መልዕክት!

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፤ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ**



**የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሆነው በመሾማቸው እንኳን ደስ ያሎት እያለ፤ መጪው የስራ ዘመንዎም የተሳካ እና የኢትዮጵያ ብልፅግና የሚረጋገጥበት እንዲሆን ይመኛል።**

## የእንኳን ደስ አደረሳችሁ መልዕክት!

**እንኳን ለ1 ሺሕ 499ኛው የመውሊድ በዓል በሠላም አደረሳችሁ!**

**በዓሉ የደስታ እና ማካፈል እንዲሆንልዎ ከልብ እንመኛለን!**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት-**

**ስብስብ አባፊራ**






Baga bacaqii gannaa hofkolee booqaa biraatti baane! Irreechi araara;araara waaqatu jaalata.

ኢረቻ እርቅ ነው ፤ ፈጣሪ እርቅን ይወዳል!

**የኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ድል ያበሰረዉን በብሔራዊ ምክር ቤት ምርጫ የምስጋና ፕሮግራም በኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት ተካሄዷል ::**

**በአገራዊ ምክር ቤት ምርጫ በጉባኤው በተላያዩ ኮሚቴነት ለተሳተፉት እና የገንዘብ ድጋፍ ላደረጉት ምስጋና ተቸሮአቸዋል**



**አሸናፊነትን ድልን ማበረታታት ለሌላ ድል እና አሻናፊነት ያናሳሳል በሚል መሪ ቃል በተዘጋጀው በዝሁ ፕሮግራም የኦሮሚያ ንግድ ምክር ቤት ቦርድ የኦሮሚያ ዘርፍ ቦርድ የከተማ ምክር ቤቶች እና ሙሉ ሰራተኞች የላቀ ምስጋና ይገባቹአል እኔንም አጋራዊ አዳራችሁን እንዲወጣ አልሀ ይርዳኝ::**





**የአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጠና ብሄራዊ የትግበራ ኮሚቴን ክቡር የንግድና ቀጠናው ትስስር ሚኒስቴር ዶር ካሣዉን ጎፊ በይፋ ስራ አስጀምሯል ::**

የትግበራ ኮሚቴው አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሚኒስቴር መስሪያቤቶች ሚኒስትር ዴኤታዎች: የብሄራዊ ባንክ ምክትል ገዢ እና የተቋማት ምክትል ኮሚሽነሮችን በውስጡ ያቀፈ ጠንካራ አደረጃጀት ነው:: በዛሬው ውይይት መድረክ የአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጠና የሙከራ ንግድ ማስፈፀሚያ እቅድ ስትራቴጂ ዝግጅት ሂደት ላይ እና በረቂቅ ደረጃ እየተዘጋጀ የሚገኘውን የቀጠናውን ተገምግመዋል ::



## የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (አይኤምኤፍ) ባለሙያዎች ጋር ውይይት አድርጓል።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (አይኤምኤፍ) ባለሙያዎች ጋር በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በተለይም የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ ዙሪያ ውይይት አድርጓል።**



**ውይይቶቹ ያተኮሩት የአይኤምኤፍ የስምምነት አንቀፅ VIIIን በመተግበር ላይ ሲሆን አራት ቁልፍ ጉዳዮችን የግሉ ሴክተር ግምገማዎችን መሰረት አድርጎ ተመልክቷል። እነዚህም ለግሉ ዘርፍ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት፣ የምንዛሪ ዋጋን መወሰን፣ የትርፍ ክፍፍል እና የወለድ ምጣኔ እና የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ሰነዶች የሚያጠቃልሉ ናቸው።**

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በምክትል ፕሬዚዳንቱ ዶ/ር አይናለም አባይነህ እንዲሁም በዋና ጸሐፊው ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ ሲወከል የአለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም (አይኤምኤፍ) ደግሞ የገንዘብ እና ማክሮፕሩደንሺያል ፖሊሲ ክፍል ኃላፊ በኢንጊብጆርግ ጉድብጃርትስዶቲር ተወክሏል።**

**የኢትዮጵያ-ቻይና (ሻንዚ) የኢኮኖሚ እና የንግድ ልውውጥ መድረክ በቶንግ ዳ ሆቴል ተካሂዷል።**

የውይይት መድረኩን ያስተባበሩት በቻይና ሲሲፒአይቲ-ሻንይ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ናቸው።

በሻንሲ ግዛት ከሚገኙ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ማለትም ከምግብና ግብርና፣ ፋይናንስ፣ ቱሪዝም፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ አቪዬሽን እና ሌሎችም የተውጣጡ ልዑካን ከኢትዮጵያውያን አቻዎቻቸው ጋር ተገናኝተዋል።







በመክፈቻ ንግግራቸው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመካከለኛው ምስራቅ እስያ እና ፓሲፊክ ሀገራትዳይሬክተር ጀነራል አምባሳደር ንጉስ ከበደ፥ ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ያላት ኢኮኖሚያዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ገልጸው በኢትዮጵያ እና ሻንዚ መካከል ያለው ፎረም በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በቱሪዝም እና በሌሎች ዘርፎች ትብብር ለማድረግ ሌላ እድል ይሰጣል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አይናለም አባይነህ (ዶ/ር) ከግብርና፣ ቱሪዝም፣ ከአቪዬሽንና ከኤርፖርት መሠረተ ልማትና ከሌሎችም ኢንዱስትሪዎች የተውጣጡ የሻንዚ የልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ ያደረገው ጉብኝት አዳዲስ ዕድሎችን ከመፍጠርም ባሻገር ከኢትዮጵያውያን አቻዎቻቸው ጋር ለመስራት ያግዛል ብለዋል።




በተጨማሪም በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት አቅም ላይ አፅንዖት ሰጥተው ያብራሩ ሲሆን ኢትዮጵያ ያላት ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ፣ ብዙ የተፈጥሮ ሃብት እና ሰፊ ገበያ ከመላው አለም ለመጡ ባለሃብቶች ተመራጭ መዳረሻ ያደርጋታል ነው ያሉት።

.......ወደ ገጽ 3 ዞረዋል

**የኢትዮጵያ-ቻይና .....የቀጠለ......** የልዑካን ቡድኑን የሚመሩት የቻይና ዓለም አቀፍ ንግድ ማስፋፊያ ምክር ቤት የሻንዚ ንዑስ ምክር ቤት የዲፓርትመንት ምክትል ኃላፊ ሚስተር ዣኦ ሹሃል ግዛቷ በቱሪዝም፣ በአቪዬሽንና በኤርፖርት መሠረተ ልማት ግንባታ፣ በግብርና፣ በሎጅስቲክስ እና ታዋቂ እንደሆነች ገልጸዋል። ይህ መድረክ ለቀጣይ ግዛቷ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በኢትዮጵያ እና በቻይና መካከል ለወደፊት ትብብር እና አጋርነት እንደ መነሻ ይሆናል ብለዋል።

በዝግጅቱ ላይ የኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች በዘርፉ ያለውን ተስፋ እና ወደፊት በሻንዚ እና በኢትዮጵያ ኩባንያዎች መካከል ያለውን ትብብር አስመልክቶ ንግግር አድርገዋል።




በኢትዮጵያ ከተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የተውጣጡ ኩባንያዎችማለትም የቆዳ ማህበራት፣ ኮንስትራክሽን፣ ጨርቃጨርቅ፣ ስጋ፣ ቱሪዝም እና ሌሎችም በፎረሙ ላይ ከሻንዚ የንግድ ተቋማት ጋር ተወያይተዋል።

ከሻንዚ የመጡ በቱሪዝም፣ በፋይናንስ፣ በፍራፍሬ፣ በአውሮፕላን ማረፊያ እና በመሠረተ ልማት የንግድ ድርጅቶች ተወካዮች ከኢትዮጵያውያን የንግድ ድርጅቶች ጋር በመተባበር መስራት በሚችሏቸው ጉዳዮች ዙሪያ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በቻይና ሰሜናዊ ምዕራብ የሻንዚ ግዛት ከ39 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያላት ሲሆን በሀገሪቱ በቱሪዝም እና በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ታዋቂ ነው።

## በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነት ትግበራ እና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ በሚቻልባቸው መንገዶች ዙሪያ ውይይት ተካሄደ፡፡

በአዲስ አበባ ኃይሌ ግራንድ ሆቴል በተካሄደው ውይይት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እንዲሁም የክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተወካዮችና የግሉ ዘርፍ የቢዝነስ ተቋማት ተወካዮችና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተገኝተዋል፡፡

በCIPE አፍሪካ፣ በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና በጀርመኑ Konrad-Adenauer-Stiftung (KAS) የተሰኘው ተቋም ድጋፍ በተዘጋጀው በዚህ ውይይት በተለይም በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነት ትግበራ ለኢትዮጵያ የቢዝነስ ዘርፍ ሊያጋጥሙ የሚችሉ እድሎችና ተግዳሮቶችን ለመለየትና ለመቅረፍ ያለመ ነው፡፡




በውይይቱ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ውቤ መንግስቱ የኢትዮጵያ ቢዝነስ በአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ስር የሚኖረውን ተጠቃሚነት ለማሳደግና ሊያጋጥሙ የሚችሉ እንቅፋቶችን በአግባቡ መረዳትና አወንታዊ እድሎችን ማስፋት እንደሚገባ አንስተዋል፡፡

ምክር ቤቱ ሁልጊዜም ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ እና የግሉ ዘርፍ ተጠቃሚነት የሚያድግበትን እድል ለማስፋት እንደሚሰራ የተናገሩት አቶ ውቤ



መሰል የአሰራር፣ ታሪፍ፣ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች፣ ተወዳዳሪነት እና መሰል ጉዳዮችን በጥናት በመለየት ተጠቃሚነትን ከፍ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የመልቲላተራል ንግድ ግንኙነትና ድርድር ሲንየር ኤክስፐርት አቶ ገብረጻድቅ ጣሰው በበኩላቸው በንግድ ተወዳዳሪ ለመሆን የአፍሪካ ንግድ ቀጠና ስምምነት አተገባበርን በአግባቡ መረዳት እንደሚገባ ጠቅሰው ኢትዮጵያ ለአፍሪካ የንግድ መግቢያ በር በመሆንና በካርጎ አገልግሎት ከሌላው የተሻለ ተነጻጻሪ እድል እንዳላት አንስተዋል፡፡

## ኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ቀነኒሳ ለሚ ከአፍሪካ ኤክስፖርትና ኢምፖርት ባንክ (አፍሪኤግዚምባንክ) የልዑካን ቡድን ጋር ተወያይተዋል።

**ኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ቀነኒሳ ለሚ ከአፍሪካ ኤክስፖርትና ኢምፖርት ባንክ (አፍሪኤግዚምባንክ) የልዑካን ቡድን ጋር ተወያይተዋል።**

**በተጨማሪም ባንኩ ከንግድ ባንኮች ጋር አጋርነት ለመመስረት ከብሔራዊ ባንክ ደንቦች ጋር በማያያዝ በንግድ ፋይናንስ፣ በኢንቨስትመንት ፋይናንሺንግ እና በአስመጪና ላኪ ርዳታ ላይ ትኩረት ለማድረግ እንደሚፈልግ አስረድተዋል።**

**በተጨማሪም ባንኩ ከንግድ ባንኮች ጋር አጋርነት ለመመስረት ከብሔራዊ ባንክ ደንቦች ጋር በማያያዝ በንግድ ፋይናንስ፣ በኢንቨስትመንት ፋይናንሲንግ እና በአስመጪና ላኪ የንግድ እንቅስቃሴ ድጋፍ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት እንደሚፈልግ አስረድተዋል።**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅመበራት ምክር ቤት ዋና ፀሀፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ እንዳብራሩት ምክር ቤቱ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት፣ የምርምርና የፖሊሲ አድቮኬሲ ስራዎችን ለማካሄድ እና የአቅም ግንባታ ተግባራትን ለማከናወን ቁርጠኛ ነው።**

**ከባንኩ ጋር በመተባበር በተለይም በምክር ቤቱ ውስጥ እየተካሄደ ካለው የዲጂታይዜሽን ጥረቶች አንጻር በትብብር መስራት እንደሚፈልግ ተገልጿል። ዲጂታይዜሽን አሁን እየተተገበርናቸው ካሉ ትላልቅ ማሻሻያዎች አንዱ ነው ብለዋል ዶ/ር ቀነኒሳ ።**

**በሌላ በኩል ባንኩ በአፍሪካ ሀገራት መካከል ኢንቨስትመንትን እና ንግድን ለማስፋፋት ቁርጠኝነት ያለው በመሆኑ፣ በአፍሪካ ውስጥ ያለውን የንግድ ልውውጥ የበለጠ ለማሳደግ ምክር ቤቱ በትብብር ለመስራት ፍላጎት እንዳለው አጽንኦት ሰጥተው ገልጸዋል።**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸኃፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ ከኢፌዴሪ የሰላም ሚኒስቴር የሰላም መሪ ስራ አስፈጻሚ ዶክተር አወቀ አጥናፉ እንዲሁም የስራ አመራር ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ መብራቱ ካሳ ጋር በሚኒስቴሩ እና በምክር ቤቱ በጋራ በሚከናወኑ የሰላም ግንባታ ስራዎች ዙሪያ ተወያዩ።**

በውይይቱ ሁለቱ ተቋማት ሰላም- ለንግድ ስራ እንዲሁም ንግድ- ለሰላም ግንባታ ባለው ሚና ላይ በቅርቡ በጋራ ሊካሄድ በታቀደው ኮንፍረንስ እንዲሁም በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት አድርገዋል።





የሰላም ሚኒስቴር የሰላም ግንባታ መሪ ስራ አስፈጻሚ ዶክተር አወቀ አጥናፉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለይም ከንግዱ ማኅበረሰብ ጋር ተቀራርቦ ለመስራትና ሀገራዊ ሰላምን የበለጠ ለማስፈን በሚኒስቴሩ እቅድ በማካተት በቁርጠኝነት እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

...... ወደ ገጽ 5 ዞረሯል

# በኢትዮጵያ የአግሪ ቢዝነስ ተግባራት እና የአውሮፓ ህብረት ከደን ጭፍጨፋ ነጻ ህግን በተመለከተ የባለድርሻ አካላት የማረጋገጫ አውደ ጥናት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

በኢትዮጵያ የአግሪ ቢዝነስ ተግባራት እና የአውሮፓ ህብረት ከደን ጭፍጨፋ ነጻ ህግን በተመለከተ የባለድርሻ አካላት የማረጋገጫ አውደ ጥናት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

በኢትዮጵያ የአግሪ ቢዝነስ ተግባራት እና የአውሮፓ ህብረት ከደን ጭፍጨፋ ነጻ ህግን በተመለከተ የባለድርሻ አካላት የማረጋገጫ አውደ ጥናት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

አውደ ጥናቱ በኢትዮጵያ በግብርና ንግድ ላይ ያተኮረ እና በአውሮፓ ህብረት በወጣውን ከደን ጭፍጨፋ ፀዳ ህግን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት በአዲስ አበባ ራዲሰን ብሉ ሆቴል ተገምግሟል።

በአውደ ጥናቱ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትን ጨምሮ ፣የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የሥራ ኃላፊዎች፣ በቡናና በሌሎች የግብርና ዘርፍ የተሰማሩ ግንባር ቀደም ኩባንያዎች ተወካዮችን ተገኝተዋል።





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ በመክፈቻ ንግግራቸው ኢትዮጵያ የአውሮፓን ገበያ ተደራሽነት ለማስቀጠል እና ለማስፋት ስለ EUDR መስፈርቶች ግንዛቤ ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

እነዚህን መስፈርቶች ማሟላት ስትራቴጂያዊ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን ጠቁመው በተለይም እንደ ቡና እና አኩሪ አተር ያሉ የኢትዮጵያ ዋና ዋና የወጪ ንግድ ምርቶችን በቀጥታ የሚነካ ነው ብለዋል።

"የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ በአውሮፓ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን የትብብር እና የተቀናጀ እርምጃ መወሰድ አለበት" ብለዋል ዶክተር ቀነኒሳ።



በደንቡ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የኢትዮጵያን የግብርና ንግድ አሰራር ከአለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር ለማጣጣም በባለድርሻ አካላት መካከል የተቀናጀ አካሄድ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ኢንጂነር አለማየሁ ንጋቱ በመዝጊያ ንግግራቸው ላይ እንደተናገሩት በኢትዮጵያ የማይበገር ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማስመዝገብ የአካባቢ ጥበቃና ዘላቂ የግብርና አሰራሮችን መተግበር ይጠይቃል።

አውደ ጥናቱ በአውሮፓ ህብረት ከደን ጭፍጨፋ ነጻ ደንብ (EUDR) ላይ የተደረገው ግብርና ስራዎች ጥናት ለግብርና ቢዝነስ እድገት ያለውን ጠቀሜታ በማሳየትና ደንቡን አክብሮ እንዲወጣ በማድረግ ላይ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑንም አመልክተዋል።

በአውደ ጥናቱ ወቅት የኢትዮጵያ የግብርና አሰራር ከአውሮፓ ህብረት ጋር የተጣጣመበት ደረጃ ላይ ያተኮሩ ጥናታዊ ግኝቶች ቀርበው የነበሩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ አስፈላጊ በሆኑ ርምጃዎች ላይ ውይይት ተደርጓል።



ግኝቶቹ ዘርፉን በዘላቂነት ለመደገፍ ያለመ ሲሆን በአውሮፓ የኢትዮጵያን የገበያ ድርሻ እና በአካባቢ ጥበቃ ላይ የተመሰረተ ምርትን በማስተዋወቅ ረገድ ዘላቂነት ያለው አሰራር እንዲከተል ለማድረግ ያግዛሉ።

አውደ ጥናቱ የኢትዮጵያን የግብርና ዘርፍ እና እየተለወጠ ከመጣው አለማቀፋዊ ደንቦችን ጋር በማጣጣም ወደ ውጭ የሚላከውን ምርት የረዥም ጊዜ ዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት አካል ነው።

"በኢትዮጵያ የአግሪ-ቢዝነስ ተግባራት እና የአውሮፓ ህብረት የደን ጭፍጨፋ-ነጻ ደንብን መከተላቸውን" በተመለከተ የተካሄደው የጥናትና ምርምር አውደ ጥናት የተካሄደው በጀርመኑ የተራድኦ ተቋም ጂ አይ ዜድ የገንዘብ ድጋፍ ነው።



## የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና.....የቀጠለ.....

የምርትና አገልግሎት ዝርዝርን ለአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ስምምነት ያሳወቀች ሲሆን ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች እንዲሁም ያሉትን የገበያ እድሎች በተገቢው መልኩ ማወቅ እንደሚገባም ጠቁመዋል አቶ ገብረጻድቅ፡፡

የCIPE የኢትዮጵያ ምክትል ዳይሬክተር አቶ አህመድ ሞሀመድ በበኩላቸው በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ሥምምነት ዙሪያ በኢትዮጵያ ያለውን የግሉ ዘርፍ ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ጥናት መካሄዱንና ከዚህ በፊትም በትግራይ፣ በሲዳማና በድሬዳዋ ውይይቶች መካሄዳቸውን አንስተው አሁንም በጉዳዩ ዙሪያ ስራዎች እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡



የ Konrad-Adenauer-Stiftung (KAS) የኢትዮጵያ ቢሮ ፕሮጀክት አስተዳደር ህይወት ታደሰ በበኩላቸው ድርጅቱ በአፍሪካ አጀንዳ 2063 ጉዳዮች እና በሌሎችም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እየሰራ ሲሆን የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነት ትግበራ ውጤታማ እንዲሆን አስላጊውን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን አንስተው ድጋፉ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል፡፡

በውይይቱ በስምምነቱ ትግበራ የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዲሁም የኢትዮጵያ ቢዝነስ እድሎችና መፍትሄዎች ዙሪያ ጥናት የቀረበ ሲሆን በጥናቱ መሰረትም ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

## የሐዘን መግለጫ

ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ዘመናቸውን በሙሉ ለአገራችን ትምህርትና ምርምር እንዲሁም ፖለቲካ ወደፊት ለማራመድ የተጉ፤ በተለይ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ በሰላማዊ ትግል የምናውቃቸው ምሁር ፖለቲከኛ ናቸው፡፡ ነፍሳቸው በሰላም እንድታርፍ እየተመኘሁ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጆቻቸውና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መፅናናትን እመኛለሁ::

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት**

**ስብስብ አባፊራ**



## ከሰላም ሚኒስቴር ጋር...የቀጠለ....

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ በበኩላቸው ምክር ቤቱ በሰላም ግንባታ ሂደት የንግዱ ማኅበረሰብ ሚና የላቀ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸው ይህንን ሚናውን የበለጠ ለማሳደግ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ሰላም በተለይም ለንግዱ ማኅበረሰብ ወሳኝ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ቀነኒሳ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማጠናከርና ኢኮኖሚያዊ መሻሻልን ለማምጣት ምክር ቤቱ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡




ሰላም- ለንግድ ስራ እንዲሁም ንግድ- ለሰላም ግንባታ በሚል የሚካሄደው ሀገራዊ ኮንፍረስንስም በሀገር አቀፍ ደረጃ ምቹ የንግድ ከባቢ ለመፍጠርና ሰላምን ለማረጋገጥ የላቀ አበርክቶ እንደሚኖረውም ዋና ጸሐፊው አብራርተዋል፡፡ የኢፌዴሪ የሰላም ሚኒስቴር የስራ አመራር ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ መብራቱ ካሳ በበኩላቸው ሰርቶ ለመለወጥም ሆነ በንግድ ውጤታማ ለመሆን ሰላም ቀዳሚው ጉዳይ መሆኑን አንስተው ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ የግሉ ዘርፍ ተዋናዮች ከመንግስት ጋር ተቀራርበው መስራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡

ሰላም- ለንግድ ስራ እና ንግድ- ለሰላም ግንባታ በሚል በሚካሄደው የጋራ ኮንፍረንስ በርካታ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች፣ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች እና ባለድርሻ አካላት እንደሚሳተፉበት በውይይቱ ላይ ተነስቷል፡፡

ከኢትዮጵያ ባለፈ ከጎረቤት ሀገራት የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችና ከሚመለከታቸው የግሉ ዘርፍ ተቋማት ጋር በሰላም ግንባታ እና የንግድ እንቅስቃሴ ዙሪያ የጋራ የውይይት መድረኮች እንደሚዘጋጁም ተጠቁሟል፡፡

በሚኒስቴሩ እና በምክር ቤቱ የጋራ ስራዎች ውይይት ላይ የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊዎች አቶ ውቤ መንግስቱ እና አቶ ጸደቀ ድጋፌ ተገኝተዋል፡፡

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአቮካዶ፣ ሽንኩርትና አኩሪ አተር ዙሪያ በሚተግበረው ፕሮጀክት ዙሪያ ውይይት አካሄደ።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአቮካዶ፣ ሽንኩርትና አኩሪ አተር ዙሪያ በሚተግበረው ፕሮጀክት ዙሪያ ውይይት አካሄደ።

በGIZ ድጋፍ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ እና በአማራ ክልሎች የሚተገበረው ፕሮጀክት በዘርፉ የሚሠሩ አምራቾች፣ ወጣቶች እና ሴቶች በተለይም እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ በሚቻልበት ጉዳይ ዙሪያ ነው ፕሮጀክቱ የሚተገበረው።




በፕሮጀክቱ እስካሁን በተከናወኑ ተግባራት ዙሪያ በተካሄደው ውይይት ላይ እንደተገለፀው ግብርናው ዋነኛ የኢኮኖሚ መሠረት ሲሆን እንደ አኩሪ አተር፣ ሽንኩርት እና አቮካዶ ባሉ ምርቶች ላይ እሴት መጨመርና ለገበያ ማቅረብ ትኩረት የሚሠጠው ነው።

ፕሮጀክቱ ምክር ቤቱን፣ የአግሪ-ቢዝነስ ማኅበራትን፣ የአባላትን አቅም ማሣደግ እንዲሁም በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ሥምምነት ትግበራ እንዲሁም በሌሎች የአቅም ግንባታ ሥራዎችና በተመረጡ ምርቶች ላይ የሚደረገው ሥልጠና ውጤታማ እንዲሆን ያግዛል ተብሏል።



ፕሮጀክቱ በሲዳማ ክልል ከ20 በላይ ሰልጣኞች ሥልጠናውን የወሠዱ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ ደግሞ 22 ሰልጣኞች በአኩሪ አተር ምርት እሴት መጨመርና ወደ ገበያ ማቅረብ በሚቻልበት እድል ዙሪያ ሥልጠና ወስደዋል። በሌላ በኩል በፕሮጀክቱ ከኦሮሚያ፣ ሲዳማ ክልሎች ባለፈ በአማራ ክልል ለሚገኙ በዘርፉ ለተሠማሩ አካላት አሥፈላጊው ሥልጠና እና ድጋፍ ለመስጠት እየተሠራ ሲሆን ፤ ለመንግስትና የግሉ ዘርፍ ምክክር የሚያግዙ ጥናቶች እንዲሁም ማንዋሎች ዝግጅትም እየተካሄደ ነው ።

በሌላም ከማምረት እስከ ገበያ ሂደት የተሰማሩ ተቋማት ዝርዝርን ከነሙሉ መረጃ የያዙ የመረጃ ቋት መዘጋጀቱም ተገልፆል ። በውይይቱ ላይ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚን ጨምሮ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ተገኝተዋል ።

## የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበር ከጂአይዜድ ቡድን ጋር በቻምበር ሲስተም ቤንችማርኬንግና ልማት ላይ ተወያይተዋል።

ሁለቱ አካላት የንግድ ምክር ቤቱን የደረጃ አሰጣጥና የእውቅና አሰጣጥ ሂደት በተመለከተ በተለይም ከ አባል ምክር ቤቶች ጋር በተገናኘ ውይይት አድርገዋል።

በውይይቱ የምክር ቤቱ ዋና ፀሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ የአገልግሎቶቹን ጥራት እና አስተዳደር አስፈላጊነት በመግለጽ በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ምክር ቤቶች ውስጥ ሊተገበሩ ከሚችሉ አለማቀፋዊ ስርዓቶችን የአገልግሎት ጥራት እና አሰራር ያለውን ጠቀሜታ አብራርተዋል።







ሁሉም ምክር ቤቶች ተመጣጣኝ የአድቮኬሲ እና የጥናትና ምርምር እንዲሁም የአቅም ግንባታና የንግድና ኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ ዓላማዎች ቢኖራቸውም እያንዳንዱ የራሳቸው የሆነ ባህሪ እንዳላቸው እና ተፅዕኖን ለመለካት የሚቻለው በጥራት አስተዳደር ስርአት መሆኑን ጠቁመዋል።



የንግድ ምክር ቤቱ የጥራት መለኪያና የጥራት አያያዝ ስርዓት ከጂአይዜድ ጋር በመተባበር ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚሰራ በውይይቱ ላይ ተነስቷል።

በስብሰባው የምክር ቤቱ ዋና ጸሃፊ ቀነኒሳ ለሚ (ዶ/ር)፣ ምክትል ዋና ጸሃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ፣ የPSD-E የፕሮጀክት ክፍል ኃላፊ ሚስተር ማርክ፣ የጂአይዜድ አማካሪ ሚስተር ኤካርድ ሼልበርገር እና ሌሎች የሁለቱም ወገኖች ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

**የኢትዮጵያ ንድና ዘርፍ ምህበራት ምክር ቤት ልኡካን በጋና አክራ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጎበኘ በግሉ ዘርፍ ልማት እና በአፍሪካ ልማት ላይ ቁልፍ ውይይትም አድርጓል።**

የኢትዮጵያ ንድና ዘርፍ ምህበራት ምክር ቤት ልኡካን በጋና አክራ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጎበኘ በግሉ ዘርፍ ልማት እና በአፍሪካ ልማት ላይ ቁልፍ ውይይትም አድርጓል።

በምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር አይናለም አባይነህ እና በዋና ፀሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ የተመራ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልዑካን ቡድን በጋና አክራ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኢምባሲ ጎብኝቷል።



ልዑኩ ከአምባሳደር ተፈሪ ፍቅሬ እና ከልዑካን ቡድኑ ምክትል ኃላፊ አምባሳደር አሳዬ አለማየሁ ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ውጤታማ ውይይት አድርጓል።

ውይይቶቹ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ማጠናከር እና የንግድ ትስስሮችን ለማሳደግ የትብብር እድሎችን በመለየት ላይ ያተኮሩ ናቸው። ውይይቱ የኢትዮጵያና የጋና የሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነትን በማመቻቸት ኤምባሲው ያለውን ወሳኝ ሚና አመልክቷል።

አምባሳደሮቹ በተሻሻለ የገበያ ተደራሽነት፣ የንግድ ማመቻቸት እና የኢንቨስትመንት እድሎች የግሉ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የተቀናጀ ጥረቶችን አስፈላጊነት አጽንኦት ሰጥተዋል። በተያያዘ የECCSA ልዑካን ቡድን ከአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና (AfCFTA) ሴክሬታሪያት እና ከጋና ብሄራዊ አፍሴፍቲኤ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ተወካዮች ጋር ተወያይቷል። ውይይቶቹ በአፍሪካ ውስጥ ያለውን የንግድ ልውውጥ ለማጎልበት እና የኢትዮጵያን ምርቶች በአህጉር ገበያ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የ AfCFTA ስምምነትን ለመጠቀም ኢትዮጵያ ባላት አቅም ዙሪያ ያጠነጠነ ነበር።





ተሳትፎው የኢትዮጵያ የንግድ ድርጅቶች በስምምነቱ የሚገኘውን ጥቅም ከፍ ለማድረግ እንዲችሉ የ ECCSA ልዑካን የኢትዮጵያን ተሳትፎ የበለጠ ለማሳደግ ስትራቴጂካዊ መንገዶችን እንዲመረምር መድረክ ፈጥሯል። ሁለቱም ወገኖች በአቅም ግንባታ ውጥኖች፣ በንግድ ፖሊሲ አሰላለፍ እና ምቹ የንግድ ሁኔታ እንዲፈጠር በመምከር የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች በአፍሪካ ገበያ እንዲበለጽጉ ለማድረግ ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል።



ጉብኝቱ የኢትዮጵያን የግሉ ዘርፍ ለማጠናከር እና በአህጉራዊ እና አለምአቀፍ ገበያዎች ያላትን ተሳትፎ ለማስፋት በሚደረገው ጥረት ወሳኝ ወቅት ሲሆን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በአፍሪካ ውስጥ ለማስቀጠል ያላመ ነው።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የልዑካን ቡድን የጋና ጉብኝቱ በሁለተኛው ቀን የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልዑካን ቡድን የጋና ነፃ ዞኖች ባለሥልጣንን ጎብኝቷል።**



ጉብኝቱ ዓላማው ስለ ጋና የነጻ ዞን ስራዎች፣ የቁጥጥር ማዕቀፎች እና ምርጥ ተሞክሮዎች ግንዛቤን ለማግኘት ነው።

በጉብኝቱ ወቅት የተደረጉት ውይይቶች የኢትዮጵያን የነጻ ቀጠና ውጥኖችን ለማሳደግ፣ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና የወጪ ንግድን ለማሳደግ እንደዚህ አይነት ሞዴሎችን እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል ላይ ያተኮረ ነበር።

የልዑካን ቡድኑ ጋና ለንግድ ስራ እድገት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር እና የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ ጋና ካገኘችው ስኬት ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው ገልጿል።





## በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርዓት የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ የሚመክር ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ አለም አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮንፈረንስ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተካሂዷል።

በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርዓት የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ የሚመክር ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ አለም አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮንፈረንስ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተካሂዷል።




"ጥራት ያለው የቴክክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት ግንባታ" በሚል መሪ ሃሳብ በተካሄደው ኮንፈረንሱ በአስር አመታት ሀገሪቷ በዘርፉ ያስመዘገበቻቸውን ውጤቶች ለወደፊት ክህሎት ግንባታ ላይ ያለውን አስተዋጽኦ እና የዘላቂ ስልጠና እና ትምህርት መርሃ ግብር (ስቴፕ III)፣ የቴሙትስ ፖሊሲ እና አስተዳደር፣ የግሉ ሴክተር ተሳትፎ እና የዲጂታላይዜሽን ሚና ለአረንጓዴ ቴ ክ ኖ ሎ ጂ ያለውን ሚና ጨምሮ በርካታ ቁልፍ መሪ ሃሳቦች ቀርበዋል።




በSTEP 3 ስር ያሉ የGOPA ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ቀርቦ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በ ኢ ት ዮ ጵ ያ ያበረከቱት አስተዋፅዖ ታይቷል።



ከተለያዩ ሴክተሮች የተወከሉ ከመንግስት ተቋማት፣ የጀርመን ኤምባሲ ተወካዮች፣ የግል ድርጅቶች እና አለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች የተገኙ ሲሆን የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ፀሐፊ አቶ ፀደቀ ደጋፌ ተገኝተዋል።

በመክፈቻ ንግግራቸው የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት በአቶ ሰብስብ አባፊራ የተወከሉት አቶ ፀደቀ ድጋፌ የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ስርዓትን በመቅረፅ ረገድ የግሉ ዘርፍ የሚጫወተውን ወሳኝ ሚና አብራርተዋል።

## የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት መቀመጫውን ዋሽንግተን ዲሲ ካደረገው የዓለም አቀፍ የግል ኢንተርፕራይዝ ማዕከል የአፍሪካ ሪጅናል ዳይሬክተር ላርስ ቤንሰን የተመራ ልኡክ ጋር ውይይት አድርጓል።

በውይይቱም የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የተዳሰሱ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የንግድ ምክር ቤት ጉዳዮች፣ የንግድ ለሰላም፣ በንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ስርዓት የሴቶች አመራር እና ዲጂታላይዜሽን ስርዓት ይገኙበታል።



የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ የንግድ ምክር ቤቱን ለሰላም መስፈን ያለውን ሚና ገልፀው ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ወሳኝ ሚና እየተጫወተ መሆኑንም ገልጸዋል።



በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዘርፍ የቢዝነስ ልማትና ሰላም ግንባታን የሚደግፉ የቀድሞ የትብብር ስራዎችን በማጎልበት ከሳይፐ ጋር ያለውን አጋርነት ለማስቀጠል ምክር ቤቱ ቁርጠኛ መሆኑን አብራርተዋል።

ስብሰባው በቀጣይ የትብብር ስራዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን ምክር ከመንግስት ተቋማት ጋር በመተባበር በስልጠና እና በመተባበር በውይይቱም የግሉ ዘርፍ እና የሰላም ጥረቶችንና ትስስርን ጋር በመተባበር ሀገር አቀፍ የቢዝነስ ለሰላም ኮንፈረንስ



ቤቱ የንግዱን ማህበረሰብ አቅም ለማሳደግ ያላሰለሰ ጥረት እንደሚያደርግም ገልጸዋል።
የበለጠ የሚያጠናክር ከሰላም ሚኒስቴር እና CIPE በሚቀጥለው ወር እንደሚካሄድ ተገልጿል።

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ለአባል ምክር ቤቶችና ማኅበራት ባለሙያዎች በዲጂታል አገልግሎት ዙሪያ ስልጠና ሰጠ።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ለአባል ምክር ቤቶችና ማኅበራት ባለሙያዎች በዲጂታል አገልግሎት ዙሪያ ስልጠና ሰጠ።

ምክር ቤቱ ለንግዱ ማህበረሰብ የሚጣቸውን የዲጂታል ኦንላይን አገልግሎት፣ አባል ምክር ቤቶች አባላትን ስለሚመዘግቡባቸው አግባቦች እንዲሁም በመረጃ አያያዥ እና ተያያዥ የዲጂታል አገልሎቶች ነው ስልጠና የሰጠው።




በተግባር በታገዘው በዚህ ስልጠና ምክር ቤቶች እና አባል ማኅበራት የአባላትን መረጃ በተደራጀ የዲጂታል አገልግሎት እንዲይዙ እንዲሁም የሚሰጧቸው አገልግሎቶች በኦንላይን መሆን እንዳለባቸውና ይህም የተቀላጠፈ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር የተደራጀ መረጃ ለመያዝ እንደሚያግዝ በስልጠናው ላይ ተገልጿል።




ስልጠናውን የሰጡት የምክር ቤቱ የአይ ሲቲ ዲቪሽን ኃላፊ ወ/ሪት ሀርያ ወልደገብርኤል እና የአይሲቲ ባለሙያው አቶ ኤርምያስ አባይ ናቸው። በGIZ-SEQUA የገንዘብ ድጋፍ በምክር ቤቱ የቢዝነስ አመራር አካዳሚ የተሰጠው ይህ ስልጠና በቀጣይም እንደሚሰጥ ተጠቁሟል።

## ኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ር ቤት ከቱርኪዬ ኤምባሲ ጋር በመተባበር በኦሮሚያ ክልል እና በቱርክ ሃገር ባሉ በምግብ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ አምራቾችና ነጋዴዎች መካከል ጋር ቨርቿል የቢዝነስ ፎረም በመስከረም 6 /2017 በተሳካ ሁኔታ ማካሄድ ችሏዓል።

የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ር ቤት ከቱርኪዬ ኤምባሲ ጋር በመተባበር በኦሮሚያ ክልል እና በቱርክ ሃገር ባሉ በምግብ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ አምራቾችና ነጋዴዎች መካከል ጋር ቨርቿል የቢዝነስ ፎረም በመስከረም 6 /2017 በተሳካ ሁኔታ ማካሄድ ችሏዓል።




የንግድ ፎረሙ ላይ በምግብ ዘርፍ የተሰማሩ አስር የሚሆኑ የክልላችን አስር የቱርክ ኩባንያዎች የተሳተፉ ሲሆን በተለያዩ መስኮች በጋራ መስራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ በስፋት ተወይተዋል።

በኦሮሚያ በኩል የተሳተፉት በአብዛኛዉ ከአዳማና ቢሾፍቱ ከተሞች የተዉጣጡ ሲሆን በቱርክ በኩልም ከቱርኪዓናቶለዒያ በምግብ ኢነዱስትሪ የተሰማሩ ኩባኒዮች ነበሩ።

የቢዝነስ ፎረሙ በኦሮሚኣ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ር ቤት ዋና ጠሃፊ አቶ እስማኤል ያሲንና የቱርክ ኤምባሲ ኮመርሻል አታሼ ም/ር ጠሃ አልፐሬን የመክፈቻና የእንኳዓን ደህና መጣችሁ አጭር ንግግር የተከፈተ ሲሆን በዚሁ መክፈቻ በአቶ እስማኢል በኩል ስለ ሮሚኣ ንግድና ዘርፍ ማ/ም/ር/ቤት ተልእኮና ስለዉይይቱ አስፈላጊነት እንዲሁም የቱርምና የክልላችን ባለሃብቶች አብሮ ለመስራት ክልሉ ያለዉን እምቅ አቅምም ጨምረዉ አብራርተዋል።

በማስከተልም በሁለቱም በኩል በፎረሙ ላይ የተገኙ ተሳታፊ ባለሃብቶች የኩባኒዮቻቸዉን ፕሮፋኢል እና በምን መልኩ አብሮ መስራት እንደሚፈልጉ ካቀረቡ በሃላ ወደ ዝርዝር ዉይይት ተገብቷዓል።

የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማ/ም/ር ቤት እና የቱርኪዬ ኤምባሲ በቀጣይም በሌሎች እንደ ጨርቃጨርቅ፣ ብረታ ብረት፣ የጥዳትና የዉበት ኢንዱስትሪ ዘርፎች በቀጣይ ሁለት ወራት ዉስጥ ተመሳሳይ ፎረም ለማዘጋጀት እቅድ የተያዘ መሆኑንና በዚህም የክልላችን አምራቾችና ነጋዴዎች ከአለማቀፍ ኩባንዮች ጋር የመስራት እድል በስፋት ለመፍጠር ለመስራት መታቀዱም ታዉቋል።

# የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ገጽታ ከውጭ ሲታይ





ኢትዮጵያ ቻምበር
ETHIOPIA CHAMBER

## የግሉ ዘርፍ ድምጽ!


**ዋና አዘጋጅ :-**

ደበበ አበበ

**ከፍተኛ አዘጋጅ :-**

ስማቸው ተበጀ

**የፎቶግራፍ ባለሙያ:-**

ያለምፍሬ በቀለ


FOLLOW US ON

www.ethiopianchamber.com

t.me/ethiopiachamber

facebook.com/EthiopianChamber

youtube.com/@ethiopianchamber

twitter.com/EthiopiaChamber

info@ethiopianchamber.com

+251115514005

Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

## The Center's Services

- ⇒ Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services
- ⇒ Internet & Electronic Resource Services
- ⇒ Support on information searching
- ⇒ Reprographic Service
- ⇒ Advising users on reference materials available in resource center.
- ⇒ Types of Materials in the Center
- ⇒ Books, Periodicals, Journals, Magazines
- ⇒ Audio and Video CD collections
- ⇒ E-Books & Publications
- ⇒ Business & Economic Statistics & Databases
- ⇒ Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)

## For further information:

*Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations ECCSA Resource & WTO Reference Center*

- ⇒ **Mexico Square, ECCSA Building**
- ⇒ **Ground Office , Room No. 13/14**
- ⇒ **Open to public Monday-Friday from 2:30 am to 5:00 pm**
- ⇒ **Tel: 251-115514005**
- ⇒ **Mob. 0966038499**
- ⇒ **Fax: 251-115517699**

